# «ኦሮሞዉ ከማንም ቢበልጥ
# እንጂ ያላነሰ ኢትዮጵያዉ ነው !

**አማኑዔል ዘሰላም**
work_amanuel@yahoo.com

ይህችን ሰሞን እያነጋገረ ያለዉ ጉዳይ ቢኖር በቅርቡ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር አመራር አባላት መካከል የተፈጠረው ክፍፍል ነዉ። በአንዳንድ መገናኛ ብዙሃን እንደተዘገበዉ ይህ ክፍፍል የኢትዮጵያ አንድነትን በመቀበልና ባለመቀበል ላይ የተነሳ ልዩነት እንደሆነ ተደርጎ ሲወራ ሰምቻለሁኝ። ነገር ግን እዉነታዉ አብዛኞቻችን ከምናስበዉና ከምንመኘዉ የተለየ ነዉ።

አቶ ዳዎድ ኢብሳ የሚመሩት ቡድንም ሆነ በጄኔራል ከማል ገልቹ የሚመራዉ፣ ኦነግ ከዚህ በፊት ከሚያራምደዉ የፖለቲካ ፕሮግራም  የተለየ ፕሮግራም የላቸዉም። ከአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ጋዜጠኛ አቶ ሰለሞን ክፍሌ ጋር በተደረገዉ ዉይይት በኢትዮጵያ አንድነት ጉዳይ ላይ ቀጥተኛ የሆነ ጥያቄ ሁለቱንም ቡድን የሚወክሉ ግለሰቦች (ዶ/ር በያንና አቶ ለንጮ ባቲን) ተጠይቀዉ ቀጥተኛ መልስ ሊሰጡ አልቻሉም።  ይህ የሚያሳየዉ ሁለቱም ቡድኖች ኢትዮጵያን እንደ አንዲት ሉዓላዊት አገር ያልተቀበሉ መሆናቸዉን ነዉ። **አንድ በሉ።**

የአቶ ዳዎድ ኢብሳ ቡድን አራት የአመራር አባላትን እንዳገደ የሚገልጽ መግለጫ አስመራ ከሚገኘዉ ጽ/ቤቱ ሲያወጣ፣ በሌላ በኩል የነ ጄኔራል ገልቹ ቡድን ከሻቢያ ጋር በቅርበት እየሰራ እንደሆነ በሰፊዉ እየተዘገበ ነዉ። እንግዲህ ይህ የሚያሳየዉ ሁለቱም ቡድኖች በተለያየ መልኩ የሻቢያ ጥገኛ እንደሆኑና ማዕከላቸዉ አስመራ እንደሆነ ነዉ የሚያሳየዉ። **ሁለት በሉ።**

ሁለቱም ቡድኖች ከዚህ በፊት ኦነግ አራምደዋለሁ በሚለዉ (ያራምድ አያራምድ ግን በማይታወቀው) በትጥቅ ትግል ስልት ላይ ለዉጥ አለን ሲሉ አልተሰሙም። በሌላ አባባል አሁንም ሁለቱም ቡድኖች እናራምዳለን የሚሉት የትጥቅ ትግልን ነዉ። እንግዲህ **ሶስት በሉ።**

ታዲያ የትላንቱ ኦነግ ከአሁኖቹ «ኦነጎች» በምንድን ነዉ የሚለየዉ ? እኔ ምንም ለዉጥ ወይንም የተሻሻለ ነገር አላየሁም።፡እንደ ትልቅ ነገር ተደርጎም ሊቆጠር አይገባም ባይ ነኝ።

እንግዲህ ስለ ኦነግ መከፋፈል ይህን ካልኩኝ በጠቅላላ ስለ ኦነግ ያሉኝን አንዳንድ  ነጥቦች ለአንባቢያን ለማቅረብ እፈልጋለሁኝ። መቼም ከፋፋይ ወይንም «ነፍጠኛ» እንደማልባል እገምታለሁኝ። የተቀዋሚ ድህረገጾችም ነጻ ሆነዉ የጻፍኩትን ያትሙልኛል ብዬ አስባለሁ። መቼም ኦነግን ወይንም የኦነግን ተከታዮች ፈርተው መልእክቴን እንደማያፍኑት ነዉ።

በመጀመሪያ ደረጃ በተለይም ኢሕአደግ አዲስ አበባ ሲገባ ያልነበርን ሰዎች ብዙም ላናዉቅ እንችላለን። ኦነግ በፖለቲካ ፕሮግራሙ ከኢሕአዴግ የባሰ እንጂ ያልተሻለ ነዉ። የብሄር መብት እስከ መገንጠል የሚለዉን፣ ኦነግ በጣም ይደግፋል። በዘር ላይ ብቻ የተመሰረተዉን ከፋፋይ ፌዴራሊዝም ኦነግ ከልቡ ያደረገዉና እንዲቀየር በጭራሽ የማይፈልገዉ ጉዳይ ነዉ። ፈረንጅ ወለድ የሆነዉን ላቲን ቋንቋን በግድ በኦሮሚያ የሚኖረዉ ሕዝባችን እንዲማር ያደረገ ኦነግ ነዉ። አስታወሳለሁ፣ በ 1991 በአዲስ አበባ ቻርተሩን ለማጽደቅ ስብሰባ ሲደረግ፣ ዶ/ር ነጋሳ ዲልቦ (የያኔዉ የኦነግ ሊቀመንበር) በኦሮምኛ አቶ ዮሐንስ ለታ (ወይንም ሌጬ ለታ) በእንግሊዘኛ ነበር የሚናገሩት። (አማራኛ ለመናገር ከመጸየፋቸዉ የተነሳ)። ኦነግ እስከአሁን ድረስ የሚያወጣቸዉን መግለጫዎች እንኳን ብታነቡ በላቲን ኦሮምኛ፣ እንግሊዘኛና አረብኛ ብቻ ነዉ የምታዩት። **ለአማርኛ ትልቅ ጥላቻ ስላላቸዉ የአረብኛን እንካን ቦታ አልሰጡትም። እንግዲህ ይህ የኦነጎችን ዉስጣዊ ጤነኛ ያልሆነ የተበላሸ አስተሳሰብ ያሳያል።**

አሁን ደግሞ መጠየቅ አለባቸዉ ወደምላቸዉ መሰረታዊ ጥያቄዎች ልመለስ። ብዙዎቻችን ኦነግን ማቀፍ አብዛኛዉን ኦሮሞ እንደማቀፍ አድርገን እናስባለን። በተለይም በዉጭ አገር የምንኖር

ኢትዮጵያዉያን። ለዚህም ነዉ ኦነግ የሚነዳዉ ሳይወለድ የሞተዉ ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ሲመሰረት በወቅቱ በባዶ ሎቤ ስንረግጥ የነበረዉ። የኦነግ ባለሥልጣናት «የኦሮሞን ሕዝብ እንወክላለን« ብለዉ በድፍረት ሲያወሩንል እኛም አምነናቸዉ «አዎ» ብለን ተቀብለን እንዲሁ በሜዳ ላይ በባዶ ስነወዛወዝ ክርመናል።

እሲቲ እዉነትን እንነጋገር። እንዴት ተደርጎ ነዉ ኦነግ የኦሮሞን ሕዝብ ይወክላል የሚባለዉ። ግራ የሚገባኝ ጉዳይ ሆኖ ስላገኘሁት የሚያሳምነኝ ሰዉ ካለ ለመማር ዝግጁ ነኝ።

መጀመሪያ «እግሌን እንወክላለን» ከተባለ «እገሌዉ» መታወቅ አለበት። ኦነግ የኦሮሞን ሕዝብ እወክላለሁ ሲል ለመሆኑ የቱ ነው የኦሮሞ ህዝብ የሚባለዉ? በምን መለኪያ ነዉ አንድ ሰዉ «ኦሮሞ» የሚሆነዉ? የመጀመሪያዉ ቋንቋ ኦሮሞኛ የሆነ ሰዉ ነዉ ኦሮሞ የሚባለዉ ? ወይስ ትዉልዱ ኦሮሚያ ዉስጥ የሆነ ? ወይስ አንድ ሰዉ «እኔ ኦሮሞ ነኝ» ካለ ያ ሰዉ ኦሮሞ ይባላል ? ወይስ የአባት ዘር እየታየ ነዉ ?

እኔን እንደምሳሌ መጥቀስ እፈልጋለሁኝ። ትዉልዴ ፊንፊኔ/አዲስ አበባ ነዉ። ፊንፊኔ ደግሞ የኦሮሚያ እንምብርት ናት። የመጀመሪያ ቁንቋዬ እንደ አብዛኛዉ የፊንፊኔ ነዋሪ አማርኛ ነዉ። ኦሮምኛ ያላወኩት ፈቅጄ ወይንም ወድጄ አይደለም። በመቱ የሚኖር የአክስቴ ልጅ ደግሞ አማርኛ መናገር እንጂ ችግር ያለበት ኦሮምኛዉን በራት እግሩ ነዉ የሚያስኬደዉ።

ኢሕአደግ አዲስ አበባ እስኪገባ ድረስ አንዱ አያቴ ሲዳሞ፣ አንዱ ሃረርጌ፣ የወንድ አያቶቼ ደግሞ ጎጃምና ሃረርጌ እንደተወለዱ ብቻ ነበር የማወቀዉ። የዘር ፖለቲካዉ ሲመጣ ሃረርጌ ያሉ የሥጋ ዘመዶቼ በኦነግ ታጣቂዎች ዉጡ መባል ጀመሩ። ያኔ ኦነግ ከኢሕአዴግ ጋር የመንግስት አካል የነበረ ጊዜ ማለት ነዉ። (የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም። ይቅር ግን ሊል ይችላል)

እኔም ከምን «ዘር» እንደሆንኩኝ መመርመርና ማጥናት ጀመርኩኝ። ከብዙ ጥናት በኋላ ከአራቱ አያቶቼ ሁለቱ ኦሮምኛ ከሚናገሩ ሕብረተሰብ የወጡ "ኦሮሞዎች" እንደሆኑ አወኩኝ። (የአዳና የነገሌ ኦሮሞዎች)። አንደኛዉ አያቴ ትዉልዳቸዉ ጎጃም ሲሆን እንደሚታወቀዉ ጎጃሜዎች የ«አማራ« እና የ«ኦሮሞ» ድብልቅ ስለሆኑ «ኦሮሞ» ወይንም «አማራ» ለማለት ከበደኝ። አራተኛዉ አያቴ በእናታቸዉ የጅማ «ኦሮሞ» ሲሆኑ በአባታቸዉ ደግሞ የመርሃቤቴ («አማራ» መሆኑ ነዉ እንግዲህ) ሰዉ ነበሩ። እንግዲህ የጎጃሜዉ አያቴ ዘር አልታወቀም እንጂ ቢያንስ ቢያንስ ከስምንቱ ቅድመ አያቶቼ አምስቱ በርግጥ «ኦሮሞዎች» ናቸዉ ማለት ነዉ።

እንግዴህ እኔ ምንድን ነኝ ? እኔ ኦሮሞ አይደለሁምን ? ወይንስ እኔ ኦሮሞ እንድባል እንደ አብዛኛዉ የኦነግ አመራር አባላት ምዕራብ ወላጋ መወለድ ወይም ከፈረንጆች ያመጡትን ላቲን ማወቅ አለብኝ?

ሌላዉ ጥያቄ የዉክልና ጥያቄ ነዉ። ኦነግ «የኦሮሞ ህዝብን« እወክላለሁ ሲል መቼ ነዉ የ«ኦሮሞ ህዝብ» ለኦነግ ዉክልናዉን የሰጠዉ ? እኔ እስከማወቀዉ ድረስ የነ ሄርማን ኮህንን ገጸ በረከት አግኝቶ፣ በ1991፣ ኦነግ በሕዝብ ሳይመረጥ የመንግስት አካል ለመሆን በቀቶ እንደነበረና መሪዎቹ ማስተዋል ጎድሏቸዉ ኃላ ቀርና ከፋፋይ ፖለቲካን ሲያራምድ ነዉ የማዉቀው ። (አቶ ሌንጮ ለታ በኢትዮጵያዊነት ላይ እንደራደር ሲሉ ትዝ ይለኛል)

ኦነግ በስልጣን ላይ በነበረ ጊዜ አሁን «ኦሮሚያ» በሚባለዉ ክልል ብዙ በዘር ላይ የተመሰረቱ እልቂቶች ተፈጽመዋል። ከምዕራብ ወላጋ ከአንድ አካባቢ የተወለዱ፣ አስተሳሰባቸዉ በሚሲዮናዉያኖች የተበረዘ በኢትዮጵያ ላይ ትልቅ ጥላቻና ችግር ያለባቸዉ በግድ የፈረንጆችን ቋንቋ (ላቲን) ሕዝብ ሳይመርጥ በሕዝብ ላይ በግድ የጫኑ ሰዎችን ያቀፈ ድርጅት ነዉ። ታዲያ አለአንዳች ሚዛን፣ አለ አንዳች መረጃ፣ ጥቂቶች ስላሉ ብቻ ኦሮሞን እንወክላለን ስላሉ እነርሱን አምነን እንደ ትልቅ ኃይል መቁጠር ኩሩ ኢትዮጵያዊን ኦሮሞን መሳደብ ነዉ።

እነ ዶ/ር መራራ ጉዲና፣ እንደ ዶ/ር ቡልቻ ደምቀሳ ቢናገሩ ያምርባቸዋል። እነ አቶ ዳዎድ ኢብሳና ጄነራል ከማል ገልቺ አፋቸዉን ቢይዙ ይሻላል። እንወክላለን ካሉ የሚወክሉት እራሳቸዉን ነዉ።

ሌላ ደግሞ ለማንሳት የምፈልገዉ የኦነግን የዉትድርና አቅም ነዉ።፡አንዳንዶቻችን ኦነግ ወታደራዊ አቅም ያለዉና ኢሕአዴግን ሊያስወግድለን የሚችል ጠንካራ ቡድን እንደሆነም አድርገን እንገምታለን። ይህም በጣም በተሳሳተ መረጃ ላይ የተመሰረተ ግምት ይመስለኛል። በኢትዮጵያ ዉስጥ በአሁኑ ጊዜ ነጻ መሬት (በተለይም በፊቅ ደቡብ  ምስራቅ አካባቢ) ተቆጣጥሮ ትንሽ እየተታኮሰ ያለዉ የኦጋዴን ነጻነት ግንባር ብቻ ነዉ። ኦነግ በኢትዮጵያ ዉስጥ ምዕራብ ወለጋን ጨምሮ ነጻ መሬት የለዉም። ያለዉ ነገር ቢኖር ከአስመራ የሚተላለፍ ቴሌቭዥንና ሬዲዮ ጣቢያ ብቻ ነዉ። ይኸዉ ሰላሳ አርባ አመታት አየን ዉጤት በማምጣት አንጻር ገና ከዜሮ አላለፈም። (ማን አለ ትሉኛላችሁ ከአቶ ኢሳያይ ጋር ከተጋጩ ወይንም ወያኔ-ኢሕአዴግ በሻቢያ ላይ ጦርነት ገጥሞ ኢሳያስን ካስወገደ ኦነግ የሚባል ነገር አይኖርም። አሁን እንደ ባዶ ብርሜል ነዉ: ያኔ የባዶ በርሜል ጩኸቱም ይጠፉል)

ለምሳሌ ጄኔራል ከማል ገልቺን ተመልከቷቸዉ። እኝህ ሰዉ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በኢሕአደግ ዉስጥ የሰሩ የጄነራልነት ማዕረግ ያገኙ ሰዉ ናቸዉ። ኦህድድ ነበሩ ማለት ነዉ። በኦነግ ዉስጥ አሁን በተፈጠረዉ ክፍፍል ጄኔራል ገልቺ የአንደኛዉ ቡድን መሪ እንደሆኑ ነዉ የሚወራዉ።

እንግዲህ አስቡት - እንዴት ተደርጎ ነዉ በአጭር ጊዜ ዉስጥ እኝህ ሰዉ የኦነግ ዋና ኮማንደር ለመሆን የበቁት? ኦነግ «ጦር ሰራዊት» አለኝ ይል አልነበረም እንዴ ? ታዲያ ሌሎች ኮማንደሮች የሉም እንዴ ? ይህ የሚያስየዉ ኦነግ ይሄ ነዉ የሚባል ወታደራዊ ኃይል እንዳልነበረዉና እንደሌለዉ፤ ወይንም ወታደራዊ ኃይሉን ገና አሁን በጄኔራል ገልቺ አማካኝነትና በአቶ ኢሳያስ እርዳታ ለመገንባት  እየሞከረ እንደሆነ ነዉ። እንግዲህ ኦነግ ለአመታት ሲያታልለን ነበር የቆየዉ ማለት ነዉ።

ድንጋይን ድንጋይ ሳርን ሳር ማለት አለበን። እኔ እንደሚመስለኛ ኦነግ ሚኔሶታ አካባቢ በሚኖሩ፣ በኢትዮጵያ ላይ መጥፎ ጥላቻ ባለባቸዉ፣ አገራችን ዉስጥ ካለዉ ነባራዊ ሁኔታ የራቁ፣ ሃምበርገራቸዉን እየበሉ በዉጭ አገር የሚቀመጡ የጥቂት ግለሰቦች ጥርቅም እንጂ፣  በኢትዮጵያ የሚወክለዉም ሆነ በሰፊዉ የሚደግፌዉ አካል ያለዉ ድርጅት አይደለም ባይ ነኝ። አንታለል።

በኢትዮጵያ ያለዉ «ኦሮሞ» በቋንቋዉና በባህሉ የሚኮራ፣ የመብትና የዲሞክራሲ ጥያቄ ያለዉ፣ ከሌላዉ ኢትዮጵያዊ ጋር የተጋባ የተዋለደ፣ እነ አባ መላን፣ ጂማ አባ ጅፋርን፣ እቴጌ ጣይቱን፣ ደጃች ባልቻ አባነፍሶን፣ ጄኔራል ተፈሪ ባንቲን፣ ጄኔራል ደምሴ ቡልቱን፣ ዶ/ር መራራ ጊዲናን፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን … የመሳሰሉትን ያፈራ ኩሩ ኢትዮጵያዊ ነዉ። ከረከሰ የዘር ፖለቲካ ጋር ምንም ግንኙነት የለዉም። **ከማንም ቢበልጥ እንጂ ያልተናነሰ ኢትዮጵያዊ ነዉ።**

ይህንን እንግዲህ የማቀርበዉ ህዝባችን በተለይም የኦሮምኛ ቋንቋና ባህል እንዲስፋፋ የምንፈልግና ኢትዮጵያ ዉስጥ ሁሉም ወገኖች እኩል የሆኑባት ኢትዮጵያን ለመገንባት የምንታገል ሁሉ እዉነታዉን አወቀን የሚበጀዉ የፍቀር፣ የአንድነት፣ የመተሳሰብ የወንድማማችነትና የኢትዮጵያዊነት አቅጣጫ እንድንይዝ ለማስቻል ነዉ። ጥቂቶች ወደቀኝና ወደ ግራ እንዲወስዱን መፍቀድ የለብንም። ስለዚህም የሚከተሉትን ይጠቅማሉ የምላቸዉን ከታች በማስቀመጥ ጽሁፌን አጠቃልላለሁ።

- «ኦሮሞ» ማለት ኢትዮጵያ እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋል። በኢትዮጵያ ዉስጥ ከ30 እስከ 40 በመቶዉ «ኦሮሞ» ነዉ። ኦሮሞን ከኢትዮጵያ መነጠል ልብን ከሰዉነት እንደማወጣት ነው። ስለሆነም ሰዉነትን ልብ-አልባ ለማድረግ ከንቱ ጥረት የሚያደርገዉን የኦነግ አይነቱን ፖለቲካ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መትፋት አለብን።

- የላቲኑ ቋንቋ የኦሮሞ ባህል አይደለም። ከሮምና ከማድሪድ የመጣ እንጂ። ኦሮምኛ በግዕዝ ፊደል የሚሰጥብነትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል። የግዕዝ ፊደላትን መማር አማርኛ፣ ትግሪኛ ኦሮምኛ ..እንዲሁም ሌሎችን ቋንቋዎችን በቀላሉ በአንድ ላይ እንደመማር ነዉ። በአንድ ድንጋይ ብዙ ወፎችን እንደመግደል ይቆጠራል። በቀላሉ ለመጻፍና ለማስተማር ያስችላል። ኢትዮጵያዉያንን የበለጠ ያቀራርባል። ኦሮምኛ የማናወቀዉ በቀላሉ ኦሮምኛን እንድንማር ያቀልልናል። የግዕዝ ፊደል እንደ ላቲኑ የበለጠ ኦሮምኛን አይገልጽም የሚሉ አሉ። እንደዉም ከላቲኑ የበለጠ በላቲን የሌሉ ፊደላት በግእዙ አሉ። (ጠ፣ ጭ፣ ቐ፣ ቀ፣ ጰ፣ ጸ፣ ዠ …) በግእዙ የሌሉ ደግሞ አዲስ ፊደል ሊፈጠርላቸዉ ይችላል። ለምሳሌ “ቨ” አዲስ

የተፈጠረ ፊደል ነዉ።

- አማራኛ ብሂራዊ ቋንቋ ነዉ። ልጆቻችን ኦሮምኛ ብቻ እንዲማሩ መደረጉ በኦሮሚያ የሚኖሩ ወገኖቻችን በኢኮኖሚ እንዳይሻሻሉና ከኦሮሚያ ዉጭ እድል እንዳይከፈትላቸዉ በር የሚዘጋ በጣም ጎጂ ፖሊሲ ነዉ።

  በትግራይ ያሉ ወገኖቻችን ትግሪኛ የሚማሩትን ያህል አማርኛም በደንብ ይማራሉ። ትግራይ እለም ያለ ገጠር ዉስጥ የሚኖሩ ተማሪዎች አማርኛ መጻፍና ማንበብ የሚችሉ ናቸዉ። ይህም እንዲሻሻሉ፣ በአዲስ አበባ፣ በድሬደዋ፣ በመላዉ የኢትዮጵያ ግዛት ሰፊ እድል ይከፍትላቸዋል። አማርኛ መማራቸዉ የበለጠ ተቀማቸዉ እንጂ የትግሪኛ ቋንቋቸዉን አልጎዳዉም። በኦሮሚያ የሚኖሩት ልጆቻችን ግን የሚያዉቅት ላቲን ብቻ ሆኖ መደረጉ የ«ኦሮሞን» ህዝብ በእጅጉ ጎድቶታል። በኦሮሚያ ገበሬ ሆኖ እንዲቀር የሚያደርግ የእጅ አዙር ጭቆና ነዉ። ይህም መቆም አለበት።

- ኦሮምኛ የመናገር መብት በኦሮሚያ ብቻ አይደለም መጠበቅ ያለበት። በመላዉ ኢትዮጵያ በርካታ የ«ኦሮሞ» ኮሚኒቲ ካሉ ትምህርት ቤቶች እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ኦሮምኛ ትምህርት እንዲሰጡ መደረግ መቻል አለበት። ለምን ጅጅጋ ወይም መቀሌ አይሆንም። የኦሮሞዎች መብት በሁሉም ቦታ መጠበቅ አለበት።

- በቅርቡ በኢትዮጵያ የተቋቋመ የፖለቲካ ድርጅቶች መድረክ አለ። ይህ መድረከ የእነ ዶ/ር ቡልቻ ደመቅሳ የኦሮሞ ፌዴራላዊስት ንቅናቄን፣ የዶ/ር መራራ ጉዲናን ሕብረት፣ የነ አቶ ገብሩ አሥራት ትግራይ አሬና፣ የኢትዮጵይ ሶማሊያ ዲሞክራቲክ ንቅናቄን እንዲሁም በግልሰብ ደረጃ አቶ ስዬ አበርሃምንና የደንቢደሎ ወለጋ የሕዝብ ተወካይ የሆኑትን ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን ያቀፈ የዉይይት መድረክ ነዉ።

  በዚህ መድረክ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የሚመራዉ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በታዛቢነት የተገኘ ሲሆን ከምርጫ ቦርድ ሕጋዊነትን እንዳገኘ ይህንን መድረክ ሊቀላቀል ይችላል የሚል ተስፋ አለ። ይህ መድረክ በኢትዮጵያ አንድነት ላይና በብሄረሰቦች እኩልነት ላይ የማያሻማና የማያወላዳ አቋም አለዉ። ይህ መድረክ በሰላማዊ መንገድ በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚንቀሳቀስ እንደመሆኑ መጠን በኢትዮጵያ ያለዉን የልብ ትርታ የበለጠ ሊያዳምጥ የሚችል መድረክ ነዉ።

  ስለሆነም ይህ መድረክ ከህዝቡ ጋር ያለ እንደመሆኑ የኦሮሞዎቹን፣ የትግሬዎችን የኢትዮ-ሶማሌዎቹን የከንበቶቹን የጉራጌዎቹን የቡድን መብት እንዲሁም በኢትዮጵያዊነት ደረጃ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሰብዓዊ መብትን ለማስጠበቅ ለሚደረገዉ ትግል አብይ ሚና በተጨባጭ ሊጫወት የሚችል ነዉ። በአስመራ የሚታዘዝ፣ ወይንም የወያኔ ኢሕአዴግ ተለጣፊ የሆነ ወይንም ማዕከሉን ኔዘርላንድ ወይም ዋሺንግተን ያደረገ አይደለም። ይህ መድረክ ዉጤት ሊያመጣ የሚችል ሊደገፍ የሚገባዉ ነዉ እላለሁኝ።

ኢትዮጵያዊ በሙሉ ካለፉት ስህተቶቻችን ተምረን፣ ለጥላቻና ለመለያየት መልዕክተኞች ጆሮዋችንን ደፈተን፣ ባህላችንና ቋንቋችን እያዳበርን በጋራ ወደፊት የምናድግበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለብን እንጂ በእነ ኦነግ አይነቶቹ ከፋፋይ ፖለቲካ ወደ ኃላ መጎተት የለብንም። **የክፍፍል ፖለቲካ፣ የዘር ፖለቲካ፣ የጥላቻ ፖለቲካ ገመድ የተበጠሰ ይሁን !**